# የመረጃ ማሕደር 1

## *. . . ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከወደፊት … ታማኝነቴን ቃል እገባለሁ . . .*

**መግቢያ**
**የአውስትራሊያ ዜግነት**

**የአውስትራሊያ የዲሞክራሲ እምነቶች**

አውስትራሊያ ውስጥ ሁሉም ሰው በአውስትራሊያ የማሕበራዊ ነሮ ሙሉ በሙሉ በመሳተፍና ዜጋ በመሆን የሚገኙ ጥቅሞችን ተጠቃሚ የመሆን መብት አለው። እኛ ሁላችንም ከሕግ በታች እኩል ሆነን ለመታየትና የማኅበራዊ ዕድሎችን እኩል ለመካፈል መብት አለን። ከፆታ፥ ከዘር፥ ከጐሳ፥ ከሃይማኖት ወይም ከባህል ልዩነቶች ነፃ እንደሆንም መጠበቅ እንችላለን።

አውስትራሊያ ልዩ ልዩ ባህል ያላቸው ሕብረተሰቦች አሏት። ይሄም ብዛት ካላቸው ልዩ ልዩ አገሮች የተለያየ አመለካከትና እምነት ያላቸው ሰዎችን ይጨምራል። እነዚህን ልዩነቶች አውስትራሊያ ትቀበላለች ታከብራለችም። ለምላሹ አዲስ መጭዎችን የምንጠይቀው እዚህ የሚያገኙትን የአውስትራሊያን ማሕበረሰብ የአኗኗር ዘዴዎችን፥ የዲሞክራሲ እምነቶችንና የሕብረተሰቡን ወጎች እንዲያከብሩ ነው።

እነዚህ እምነቶች የራሳችን የሆኑ አመለካከቶችን እንድንገልጽ ሙሉ መብት ይሰጡናል። የሌሎች ሰዎች አመለካከቶች ከኛ የተለየ ቢሆንም የራሳቸውን አመለካከት የመግለጽ መብት እንዳላቸው አምኖ መቀበል ይጠበቅብናል። የአውስትራሊያን ሕጎች እንድናከብርና ጠንካራና የተባበረች አገር ሆና እንድታድግ አስተዋጾ ለማድረግ ቃል ኪዳን መግባት ይጠበቅብናል።

**የአውስትራሊያ ዜግነት ሃላፊነቶችና መብቶቹ**

የአውስትራሊያ ዜጋ ለመሆን ሲወስኑ፥ ሥነ ሥርዓትን ተከትለው ከአውስትራሊያ ሕዝብ ጋር አብረው መኖር ሲጀምሩ አዲስ ሃላፊነቶችንና መብቶቹ ይቀበላሉ። የአውስትራሊያ ዜጋ መሆን ማለት አውስትራሊያዊነት መሆንና ጥቅሞችዋን ሁላችንም አብረን የምንካፈልበት አገር እንድትሆን ለማድረግ መርዳት ማለት ነው።

አዲስ የአውስትራሊያ ዜጋ በመሆንዎ የሚከተሉት ሃላፊነቶች ይኖርዎታል፥

- ሕግችን ማክበር፥
- በምርጫ መዝገብ (Electoral Roll) ላይ መመዝገብና በፌደራል (Federal) ና በስቴት (State) ምርጫዎች፥ በሕዝብ ውሳኔዎች (referendum) ላይ ድምፅ መስጠት፥
- ከሌሎች ሰዎች ጋር ሆነው ፍርድ ቤት ውስጥ የዳኝነት ውሳኔ ጁሪ (jury) እንዲሰጡ ቢጠሩ መቅረብ ፥
- አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ አውስትራሊያን መከላከል (በዚህ ረገድ አውስትራሊያ ውስጥ የተወለደ ሰው ያለው መብቶችና ነፃ የሚሆንባቸው ነገሮች ሁሉ እርሶዎም ይኖርዎታል)።

የአውስትራሊያ ዜጎች ተጨማሪ መብቶች አሏቸው። እነዚህም መብቶች የሚከተሉትን ይፈቅዳሉ፥

- የአውስትራሊያን መንግስት እንዲመረጥ ለመርዳት ድምፅ መስጠት
- የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ለሥራ ማመልከት ወይም ለሕዝብ መቀመጫ ቦታዎች ማመልከት
- ለአውስትራሊያ ፓስፖርት ማመልከት፥ ያለ ቋሚ መመለሻ ቪዛ (resident return visa) ወደ አውስትራሊያ ለመግባትና ከአውስትራሊያ ለመውጣት
- ውጭ አገር በሚኖሩበት ወቅት ከአውስትራሊያ የዲፕሎማት ተወካዮች ለደህንነትዎ ጥበቃን መጠየቅ
- በአውስትራሊያ የጦር ሠራዊት ውስጥና የአውስትራሊያዊ ዜግነት በሚጠይቁ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ እንዲመዘገቡ ማመልከት
- ማንኛውንም ልጅ (ከ 18 ዓመት በታችና ውጭ አገር የተወለደ ከሆነ) በትውልድ (by descent) የአውስትራሊያ ዜጋ አድርጎ ማስመዝገብ

**የአውስትራሊያ ዜጋ መሆን**

ከአውስትራሊያ ቋሚ ኗሪዎች (Permanent residents) ወይም ከአውስትራሊያ ዜጋ የሚወለዱ ልጆች በትውልድ የአውስትራሊያ ዜጋ ይሆናሉ። ከሌላ ቦታ ወደዚህ የመጡ ከሆነ የአውስትራሊያ ዜግነት እንዲሰጥዎት ማመልከት ይችላሉ። ከ16 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ካልዎት በማመልከቻዎ ውስጥ አብረው ሊያስገቧቸው ይችላሉ፥ እርስዎ ዜጋ በሚሆኑበት ጊዜ እነርሱም አብረው ዜጋ ይሆናሉ።

የአውስትራሊያ ዜጋ መሆን የሚችሉት፥

- ቋሚ ኗሪ ከሆኑ (Permanent resident)
- ባለፉት አምስት አመታት ቢያንስ ሁለት አመት እዚህ ከኖሩ፥ ይሄም ካለፉት ሁለት አመታት ቢያንስ 12 ወራትን ይጨምራል
- እዚህ ለመኖር ማቀድ ወይም ከአውስትራሊያ ጋር የቅርብ ግኑኙነትን ማድረግ
- ከ 18 ዓመት በላይ ከሆኑ
- መልካም ጠባይ ካልዎ
- መሠረታዊ እንግሊዝኛ ቋንቋን መናገርና መረዳት የሚችሉ ከሆነ
- የአውስትራሊያን ዜግነት ሃላፊነትና መብቶች የሚረዱ ከሆነ

## የአውስትራሊያ ዜግነት ቃል ኪዳን

የአውስትራሊያ ዜግነት እንዲሰጥዎት ከዚህ በታች ያለውን ቃል ኪዳን መግባት ይኖርብዎታል፥
ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከ ወደፊት *በፈጣሪ ስር
የዲሞክራሲ እምነቱን ለምጋራው፥
መብቱንና ነፃነቱን ለማከብረው፥
ሕጉን ከፍ አድርጌ ለማየውና ለምታዘዘው፥ ለአውስትራሊያና ለሕዝቧ ታማኝ መሆኔን ቃል እገባለሁ።

* ቃል ኪዳን ሲገቡ ከፈለጉ 'በፈጣሪ ስር' የሚለውን ቃል መተው ይችላሉ።